**ግልፅ ደብዳቤ**


## ዓለም አቀፍ የአማራ ሕብረት
**11303 Amherst Ave, Suite 2 . Silver Spring, MD 20902**
**GAC.DCmetro@gmail.com**


**ቁጥር ጠ.15/0012**
**መጋቢት 15 ቀን 2012**

ለክቡር የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር፤ ዶ/ር አብይ አህመድ
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

ጉዳዩ፡- በአማራ ሕዝብ ላይ በኃይልና በግፍ እየተካሄደ ያለው ጥቃት በአስቸኳይ እንዲቆም በጥብቅ ለመጠየቅ

የአማራ ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ ለረጅም ዘመናት ከሌሎች ወገኖቹ ጋር በመሆን የኢትዮጵያን ታሪክ በመጠበቅና ሀገራችንን በመገንባት ሂደት የከፈለውን መስዋእትነትና ያለፈባቸውን ውጣ ውረዶች ክቡርነትዎ ጠንቅቀው እንደሚያውቁት እሙን ነው። ሆኖም ላለፉት በርካታ አመታት በተለይም በወያኔ-ኢሓዴግ ሥራዓተ አገዛዝ በተረት-ተረትና በበሬ ወለደ ትርክት ታሪኩ፣ ክቡር መስዋእትነቱ፣ ሃይማኖቱና ማንነቱ ኮስሶ እንዲታይ በተቀነባበረ ስልት ሲሰራበት ከመቆየቱም በላይ ይኸው አፍራሽ ተግባር ዛሬም ሳይገታ በተከታታይ ተባብሶ መቀጠሉ እጅግ አሳዛኝ እንቆቅልሽ መሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም። በዚህ ረገድ በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንኳን የአማራ ሕዝብ በሚኖርባቸው አካባቢዎች ብጥብጥ በመቀስቀስ እንዲፈናቀል፣ ቤት ንብረቱ እንዲወድሙና ሕይወቱ በግፍ እንዲቀጠፍ ከመደረጉም በላይ በረቀቀ ሴራና ስልት በሁሉም መስክ ታግለው እያታገሉ እንደሚመሩት ተስፋ የጣለባቸው መሪዎቹ እየተገደሉ መሆናቸው ሁነኛ ማሳያዎች ናቸው።

የአማራውን ሕዝብ በጠላትነት በፈረጁ የተለያዩ አካላት የሚደቅኑትን የጥፋት ተልእኮ ለመመከት የሚያስችሉትን መንገዶች በጥንቃቄና በሰላማዊነት ለመተግበር እየተጣጣረ ያለውን ወገናችንን በዚህ በለውጥ ጊዜ መንግስት ኢሕአግና ሰላምን ከማስከበር አልፎ በአማራው ላይ የኃይል ርምጃ እየወሰደ መሆኑ ለማመን የሚከብድ ሆኖ ይታየናል። መንግስትዎ የሚመራው የለውጥ ሂደት የመጣው ራስዎ በየመድረኩ እንደመሰከሩት በሓቀኛ ፋኖ፣ ቄሮና ዘርማ በመሳሰሉ በአብዛኛው የወጣቱ ኃይል በመስዋእትነት በመራው ሕዝባዊ ትግል መሆኑ የሚዘነጋ አይደለም። መጋቢት 10 ቀን 2012 ዓ.ም ሙሉ ሌሊትና በማግስቱም ጭምር በታላቋ ና ታሪካዊት የጎንደር ከተማና አካባቢዋ የዘመተው በከባድ መሳሪያዎች የታጀበ የተኩስ ተግባር በመንግስት ኃይሎች እንደሆነና አላማውም ፋኖ በመባል የሚታወቀውን ለአማራው ፍትሕ፣እኩልነት፣ ለኢትዮጵያ አንድነት ሉአላዊነትና

፣እንዲሁም ለድሞክራሲና፣ለሕዝብ ሰላም መከበር የቆመ የወጣት ኃይል ላይ ጥቃት ማድረስ በመሆኑ መላውን አማራና የኢትዮጲያን ሕዝብ ያስቆጣ መሆኑን ልናስገነዝብዎት እንገደዳለን ።

እርስዎ የጦር ኃይሎች አዛዥ ከመሆነዎም በላይ "መግደል መሸነፍ ነው" እያሉ በማስተማርዎ የሰላምና የወደፊት ሕይወት ብሩህነትን የአገር ግንባታንና ብልፅግናን እያለሙ ያሉ ወጣቶችን በወታደራዊ ኃይል እንዲቀጠፉ ማድረግ ለወለዷቸው እናቶቻቸው መሪር ሃዘን ለህብረተሰቡ አሳፋሪና አለም ቀአፋዊ ህግ የጣስ እርምጃና ግፍ ሲሰራ አላውቅም ቢሉ አሳማኝ አይሆነም። በመሰረቱ ፋኖን ሕዝቡ የሚመለከተው በሰላም አስከባሪነት፣ ከጥቃት ተከላካይነትና በአለኝታነት የቆመለት ወጣት ልጁ አድርጎ እንደሆነ የሚሰወር ጉዳይ አይደለም። ይህን ጠንቅቀው የሚያውቁት የአማራ ሕዝብ ጠላቶች ፋኖን ማለትም የወደፊት የአማራው መሪዎች የሚወጡበትን ወጣት ኃይል እንዲመታ እያቀነባበሩት ባለው ስውር ሴራ የክልሉም ሆነ የፌዴራል መንግሥት ተባብሮ እንዲህ አይነቱን ጥቃት ይሰነዝራል ብሎ ማመን እጅግ የከበደ ከመሆኑም በላይ ነውርና የሚወገዝ ተግባር መሆኑን መግለጽ ተገቢ ይሆናል። ድርጊቱንም በጽኑ እናወግዛለን። የፋኖው ኃይል ምን ጥፋት እንደተገኘበት ሕዝቡ መክሮና ዘክሮ ይፋ ባልተድረገበት ሁኔታ ለጥፋት የቆሙ መሰሪና እኩይ ወገኖች አዘውትረው በሚሸርቡት ሴራ በሁሉም የአማራ የማንነት መግለጫዎች ላይ መዝመት ለጊዜው አጥቂነትን ቢያሳይም የኋላ ኋላ የሚያስከፍለው ዋጋ እጅግ የከበደና ይህም ሩቅ እንዳልሆነ መገንዘብ ጠቃሚ ይመስለናል። ይህ አስከፊ ጥቃት በአማራው ላይ እየድረሰ ሳለ የክልሉን ሥልጣን የያዙት ወገኖች ተባባሪና አስፈጻሚ መሆናቸው ደግሞ በታሪክና በትውልድ ፊት ይቅርታ የሌለው ክህደት መሆኑን ሊያውቁት ይገባል።

በአሁኑ ወቅት ዓለምን እያሸበረ ያለው አስከፊ የኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ በአገራችንም ተከስቶ እያለና ሁሉንም ዜጋ በማስተባበር ሕዝባችንን ከእልቂት መታደግ ሲገባ የማይመስልና "በፋኖ ስም ወንጀል የፈጸሙ ስላሉ" በሚል የፌዝ በሚመስል አካሄድ በወገኖቻችን ላይ የሚካሄደው የግፍ በትር በአፋጣኝ ሊቆም ይገባዋል። በሌላም በኩል በዚህ አስጨናቂ ወቅት የታላቁ ሕዳሴ ግድብን ምክንያት በማድረግ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ለጥቃት ዙሪያውን እያኮበኮቡ መሆኑ በግልጽ እየታየ መላውን ሕዝብ በተለመደው የአንድነት መንፈስ ለማስተባበርና ለማሰለፍ መጣጣር ሲገባ ለዚህም ዋና ጉዳይ ፋኖ እጅግ አስፈላጊ ኃይል መሆኑ እየታወቀ የማይገባ ዘመቻ ሊካሄድበትም ሆነ ለጥቃት ሊጋለጥ ይገባዋልን?

በበርካታ የሀገራችን አካባቢዎች ጽንፈኛ ቄሮን በማነሳሳት በአማራው ሁሉ አቀፍ ማንነት ላይ ሲዘመትበት በመንግስት በኩል ተገቢ የሚባል ምንም ርምጃ እንዳልተወሰደ በይፋ እያየን ዛሬ በፋኖ ላይ እየተካሄደ ያለው ዘመቻ ጋር ሰናነጻጽረው በተደጋጋሚ ዛሬም እንደትናንትናው ሴረኞቹ የአማራን ዘር ለማጥፋት ያልተኙ እንደሆኑ ያመለክታል። ስለሆነም በሁሉም የአገራችን አካባቢዎች በተለይም በጎንደር በአሁኑ ጊዜ እየተፈጸሙ ያሉት ጥቃቶች፦

1. ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲቆሙና ሕዝቡን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ የሃይማኖት አባቶችን፣ የፋኖና ሌሎችም ወጣቶች፣ሴቶች፣እንዲሁም፣ምሁራን የሚሳተፉበት መድረክ ተመቻችቶ በውይይትና በመግባባት በፋኖም ሆነ በአማራው ሕዝብ ለረጅም ጊዜያት ሲቀርቡ የቆዩ የማንነትና ሌሎችም አንገብጋቢ ጥያቄዎች አፋጣኝና ዘለቄታዊ መፍትሔ ምላሽ ተሰጥቷቸው እልባት እንዲያገኙ እንዲደረግ፣
2. የአገራችን የመከላከያ፣ የፖሊስና የጸጥታ ኃይሎች ከሕዝቡ ጎን ቆመው አማራው ለጥቃት እንዲጋለጥ ሌት ተቀን እኩይ ሴራ የሚሸርቡበትን መሰሪዎች በመያዝ ለሕግ በማቅረብ ከሕዝቡ ጎን እንዲቆሙና ንጹሓንን ከጥቃት እንዲታድጉ መመሪያዎ እንዲደርሳቸው፣
3. "በፋኖ ስም ወንጀል የፈጸሙ አሉ" በሚል ሰበብ በ 5 ቀናት ውስጥ እጃቸውን እንዲሰጡ ሲል በአማራ ክልል የጎንደር ዙሪያ አስተዳደር ያወጣው የማስጠንቀቂያ አዋጅ በፋኖ አጠቃላይ ህልውና ላይ ያነጣጠረና የክልሉን የጸጥታ ሁኔታ ወደመጥፎ አቅጣጫ ሊመራ እንደሚችል ግንዛቤ ውስጥ

በማስገባት መሣሪያ ፈትተው እጃቸውን እንዲሰጡ የሚጠይቀውን አዋጅ አጥብቀን እንቃወማለን፤

4. እስካሁን በግፍ ለተጠቁት ወገኖች አስፈላጊው ሕጋዊ ማጣራት ተደርጎ ካሳና መልሶ ማቋቋሚያ እንዲሰጣቸው በታላቅ አጽንኦት እንጠይቃለን፤

እኛ በዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት ሥር የተሰባሰብን የአማራ ተወላጆችና ደጋፊዎች ወገናችን ከማንነት ጥቃት ተላቆ በሰላምና በነጻነት ክሌሎች ወገኖቹ ጋር ድህነትን ለማስወገድ በሚያደርገው ጥረት ሁሉን አቀፍ እገዛ ለማድረግ ዝግጁ መሆናችን ይታወቃል። ይሁንና በወገናችን ላይ እየተካሄደ ያለው ጥቃት የሚቀጥል ከሆነ በማንኛውም ትግሉ ጎን ያለማወላወል የምንሰለፍ መሆኑን ለክቡርነትዎ አስረግጠን እንገልጻለን። ሁኔታውንም ለዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች፣ ለሚመለከታቸው የልማት አጋር ሀገሮችና የአለም አቀፍ መድረኮች በማሳወቅ አበክረን የምንከታተል መሆኑን ከወዲሁ እንዲገነዘቡልን እንፈልጋለን።

ዘወትር ከራሳቸው ሥልጣንና ጥቅም ውጭ የማይታያቸው መሰሪዎች ጋር በመተናነቅ ለወገን ክብር፣ ነጻነትና ማንነት መረጋገጥ ስለ ሓቅ ለወገናችን ከሚታገሉት ወገኖቻችን ጎን መሆናችንንም በዚሁ አጋጣሚ ለሁሉም ወገን በአክብሮት እንገልጻለን።

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ታፍራና ተከብራ ትኖራለች!!

ዶ/ር አምባቸው ወረታ
የዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት ሊቀ መንበር

ግልባጭ፡-

ለኢፌዲሪ ፕሬዜዳንት ወ/ሮ ሣህለወርቅ ዘዉዴ; አዲስ አበባ

ለኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ደመቀ መኮንን; አዲስ አበባ

ለኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ; አዲስ አበባ

ለኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዘዳንት ወ/ሮ መአዛ አሸናፊ; አዲስ አበባ

ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ዳንኤል በቀለ; አዲስ አበባ

ለአማራ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳደር አቶ ተመስገን ጥሩነህ;
ባሕርዳር

በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሰደር አቶ ፍጹም አረጋ
ዋሽንግተን ዲሲ

ለሰብአዊ መብት ጉባኤ አቶ ቢኒያም አባተ፤ አዲስ አበባ

ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ማኅበር ዋና ዳይሬክተር አቶ ያሬድ ኃይለማርያም
ብረሰልስና ጀኔቫ